# ገሃነም ምንድን ነው? ወዴትስ ነው ያለው?

**ዋና ጥቅስ፡**

"እነሆ፥ በቶሎ እመጣለሁ፥ ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ።" ራዕይ 22፡12 ባለፈው ትምህርታችን ስለ ዘላለማዊው የጻድቃን ቤት ተምረናል። እነዚያ ኢየሱስን አዳኛቸው መሆኑን የተቀበሉና ትዕዛዛቱን የሚታዘዙ ሁሉ ከርሱ ጋር ለዘላለም ይኖራሉ። ኢየሱስ ለሰው ሁሉ ታዛዥ ሆኖ ከመዳን ወይም በኃጢአት ጸንቶ ከመጥፋት አንዱን እንዲመርጥ ምቹ ጊዜ ሰጥቶታል።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለሚያስተምረው ነገር የማይጠነቀቁ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች አሉ። ኢየሱስን አይሰሙም፤ ትዕዛዛቱንም አይታዘዙም። በኃጢአታቸው እንዳሉ ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሊወስዳቸው አይችልም። እንግዲያውስ እነዚህ ሰዎች የሚያጋጥማቸው ምንድን ነው? ለዚህ ጥያቄ መልስ ስንፈልግ ማድረግ የሚገባን የሰውን ቃል መቀበል ሳይሆን መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ዋና ዋና ጥያቄ ሁሉ የሚያስተምረውን በትክክል ለማወቅ መበርታት ነው። እግዚአብሄር ብቻ ነው መልስ ሊሰጠን የሚችል።

1. **አሁን በገሃነም ያሉት ስንት ናቸው?**

አብዛኞቹ ሕዝቦች በየትኛው መንገድ ነው የሚጓዙት? "በጠበበው ደጅ ግቡ፤ ወደ ጥፋት የሚወስደው ደጅ ሰፊ መንገዱም ትልቅ ነውና፡ ወደ እርሱም የሚገቡ ብዙዎች ናቸውና፤ ወደ ህይወት የሚወስደው ደጅ የጠበበ መንገዱም የቀጠነ ነውና የሚያገኙትም ጥቂቶች ናቸው።" ማቴ 7፡ 13-14 እነዚህ አሳዛኝ የሆኑ ቃላት በየሱስ የተነገሩ ናቸው። ከመልካሞቹም ሰዎች ይልቅ ኃጢአተኞ ሰዎች በዓለም ላይ በጣም የበዙ ናቸው። ሆኖም ግን የቀናውን መንገድ የማይከተል ሁሉ ይጠፋል። ለመንግስተ ሰማያት መዘጋጀትን ችላ የሚሉ ሁሉ ሊድኑ አይችሉም።

በዓለም ያሉ አብዛኞቹ የሃይማኖት ሰዎች ኃጢአተኛ ሰው በሞተ ጊዜ ወዲያው ከዘላለም እስከዘላለም ወደሚሰቃይበት ገሃነም ወደተባለው ስፍራ ይሄዳል ብለው ያስተምራሉ። ይህን ትምህርት ደግሞ የአረማውያን ሃይማኖት ተከታዮች ለብዙ አመታት ሲያስተምሩ ቆይተዋል። ከብዙ መቶ አመታት

በፊት ይህ የሐሰት ትምህርት ወደ ክርስቲያን ቤተክርስቲያን ገባ። ጥያቄው ግን እንዲህ ነው፡ መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚህ ጉዳይ ምን ያስተምራል?

በእሳት መቀጣት ወዲያው በሞት ጊዜ ይጀምራልን? ወይስ ከዚያ በኋላ ነው? "አሁን ያሉ ሰማያትና ምድር ግን እግዚአብሔርን የማያመልኩት ሰዎች እስከሚጠፉበት እስከ ፍርድ ቀን ድረስ ተጠብቀው በዚያ ቃል ለእሳት ቀርተዋል።" 2ጴጥ 3፡7 ጴጥሮስ ይህ ኃጢአት የሞላበት ዓለም በእሳት የሚነጻው ገና ለወደፊት መሆኑን በግልጽ ይናገራል። ጳውሎስም በሐዋ ስራ 24፡25 ከሃጢአተኛው ገዢ ጋር ሲነጋገር "ስለሚመጣው ፍርድ" በመከረው ምክር ላይ ተመሳሳይ ነገር ያስተምራል። ኃጢአተኞች እስከሚፈረድባቸው ቀን ድረስ በእሳት መጥፋት የለባቸውም።

2. **ኢየሱስ ኃጢአተኞች መቼ ይቀጣሉ ይላል?**

   "የሰው ልጅ ከመላእክቱ ጋር በአባቱ ክብር ይመጣ ዘንድ አለውና፤ ያን ጊዜም ለሁሉ እንደ ሥራው ያስረክበዋል።" ማቴ 16፡27። ይህ ጥቅስ እንደ መግቢያ ጥቅሳችን ሁሉ ኢየሱስ ከመላዕክቱ ጋር እስኪመጣ ድረስ ማንም ዋጋውን እንደማይቀበል ይናገራል። ስለዚህ ኃጢአተኞች አሁን የሚገኙት "ገሃነም" በተባለው ስፍራ ውስጥ አይደለም።

   "እኔ የተናገርሁት ቃል እርሱ በመጨረሻው ቀን ይፈርድበታል"ዮሐ 12፡ 48። እዚህም ላይ እንደገና ኢየሱስ ኃጢአተኞች በመጨረሻ ቀን (በዓለም ፍጻሜ) እንደሚቀጡ በግልጥ ይናገራል።

3. **እሳት ኃጢአተኞችን ሁሉ የሚያጠፋው መቼ ነው?**

   "እንክርዳዱ የክፉው ልጆች ናቸው የዘራውም ጠላት ዲያቢሎስ ነው፤ መከሩም የዓለም መጨረሻ ነው፤ አጫጆችም መላዕክት ናቸው። እንግዲህ እንክርዳድ ተለቅሞ በእሳት እንደሚቃጠል በዓለም መጨረሻ እንዲሁ ይሆናል።" (ማቴ 13፡38-40 )

አንድ ሰው “ኃጢአተኞች አሁን ገሃነም በተባለው ስፍራ ውስጥ የሚቃጠሉ ይመስልሃን?” ብሎ ቢጠይቅህ “አይደለም ኃጢአተኞች በእሳት የሚጠፉት በዓለም ፍጻሜ ነው ብለህ ልትመልስ ትችላለህ።”

4. **ኢየሱስ ወደፊት የሚከሰተው ትልቁ ሁኔታ ምንድን ነው ይላል?**

“በመቃብር ያሉቱ ሁሉ ድምፁን የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል፤ መልካምም ያደረጉ ለሕይወት ትንሣኤ ክፉም ያደረጉ ለፍርድ ትንሣኤ ይወጣሉና በዚህ አታድንቁ።” ዮሐ 5 ፡28-29

ካሁን ቀደም ኃጢአተኞች በገሃነም ውስጥ የነበሩ ከሆነ በትንሣኤ ቀን ከመቃብራቸው እንዲወጡ መጥራት ለምን ያስፈልጋል? በገሃነም ውስጥ ለብዙ መቶ አመታት ወይም ሺህ አመታት ከቆዩ በኋላ በዓለም ፍጻሜ ለፍርድ የሚነሱት ለምንድን ነው? ይህ ፈጽሞ የማይሆን ነገር ነው። ኢየሱስ ኃጢአተኞች ቅጣታቸውን ለመቀበል በትንሣኤ እስከሚነሱበት ቀን ድረስ በመቃብር ውስጥ እንደሚተኙ ያስተምራል። በመሆኑም አሁን በገሃነም ውስጥ እየተሰቃዩ አይደለም።

5. **መጽሐፍ ቅዱስ ስለኃጢአተኞች የመጨረሻ ቅጣት ምን ያስተምራል?**

“የቀሩቱ ሙታን ግን ይህ ሺህ ዓመት እስኪፈጸም ድረስ በሕይወት አልኖሩም። … ወደ ምድርም ስፋት ወጡ የቅዱሳንንም ሰፈርና የተወደደችውን ከተማ ከበቡ፤ እሳትም ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ወርዳ በላቻቸው። ያሳታቸውም ዲያብሎስ አውሬውና ሐሰተኛው ነቢይ ወዳሉበት ወደ እሳቱና ወደ ዲኑ ባሕር ተጣለ፥ ይህም የእሳት ባሕር ሁለተኛው ሞት ነው። በሕይወትም መጽሐፍ ተጽፎ ያልተገኘው ማንኛውም በእሳት ባሕር ውስጥ ተጣለ።” ራዕይ 20፡5፣9፣10፣14፣15 በእግዚአብሔር ላይ በማመጽ ጸንተው የኖሩ ኃጢአተኞች በሁለተኛው ትንሣኤ ይነሳሉ። ቅጣታቸውንም የሚቀበሉት በዚሁ ምድር ላይ ነው። እንግዲህ ዛሬ እሳት የሚነድበት “ገሃነም” የተባለ ስፍራ የለም። ጌታ ዓለምን ከኃጢአት ለማንጻት በፍርድ ቀን  የሚጠቀምበት እሳት ኃጢአተኞችን ይበላቸዋል።

6. **ኃጢአተኞች ሲቃጠሉ ምን ይሆናሉ?**

"እነሆ፥ እንደ ምድጃ እሳት የሚነድድ ቀን ይመጣል፤ ትዕቢተኞችና ኃጢአትን የሚሠሩ ሁሉ ገለባ ይሆናሉ፤ የሚመጣውም ቀን ያቃጥላቸዋል፥ ሥርንና ቅርንጫፍንም አይተውላቸውም፥ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር። ...በምሠራበት ቀን በደለኞች ከእግራችሁ ጫማ በታች አመድ ይሆናሉና እናንተ ትረግጡአቸዋላችሁ፥ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር።" ሚልክያስ 4፡1፣3። ኃጢአተኞች ፈጽመው ይቃጠላሉ።

ሰዎች ኃጢአተኞች በገሃነም እሳት ከዘላለም እስከዘላለም እንደሚቃጠሉ ሲገልጹ ስለሚያስፈሩት ነገሮች የጻፏቸውን ጥቂቶቹን ነገሮች ታነብ ይሆናል። መጽሐፍ ቅዱስ ግን የጠፉት ኃጢአተኞች በፍጹም እንደሚጠፉ ነው ገልጾ የሚያስተምረው። በዮሐንስ ወንጌል 3፡36 የጠፉት "ሕይወትን አያዩም" ይላል። ለኃጢአት ቅጣቱ መንቃት ፈጽሞ የሌለበት የዘላለም ሞት ነው (ሁለተኛው ሞት)።

ለኃጢአት የመጨረሻ ገደብ ለማድረግ እግዚአብሄር ኃጢአተኞችን ፈጽሞ ማጥፋት ይገባዋል። እግዚአብሄር የፍቅር አምላክ በመሆኑ ኃጢአተኞችን ያለ ወሰን በማሰቃየት አይደሰትም። የጠፉትን ለዘላለም ማሰቃየት ቅን ፍርድ አይሆንም። ከሚጠፉት አንዳንዶቹ የባሱ በደለኞች ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ ኢየሱስ አዳኛቸው መሆኑን ላለመቀበል ችላ ያሉ ናቸው። ታድያ ሁሉም በተመሳሳይ ሁኔታ በገሃነም እሳት እንዲቃጠሉ ማድረግ ተገቢ ይሆናልን?

7. **ምድርን ከኃጢአትና ከኃጢአተኞች የሚያነጻው እሳት ምን ይሆናል?**

"እነሆ፥ እንደ እብቅ ይሆናሉ፥ እሳትም ያቃጥላቸዋል ሰውነታቸውንም ከነበልባል ኃይል አያድኑም፤ እርሱም ሰው እንደሚሞቀው ፍም፥ ወይም በፊቱ ሰው እንደሚቀመጥበት እሳት ያለ አይደለም" ኢሣ ይያስ 47፡14።

ኃጢአተኞች በሚጠፉበት ጊዜ ምንም እሳት ወይም አንዲትም ፍም ከሰል እንኳን አይቀርም። ዳዊት እንዲህ ይላል፡፡ “ኀጥአን ግን ይጠፋሉ፥ የእግዚአብሔር ጠላቶች በከበሩና ከፍ ከፍ ባሉ ጊዜ እንደ ጢስ ይጠፋሉ። … ገና ጥቂት፥ ኃጢአተኛም አይኖርም፤ ትፈልገዋለህ በታውንም አታገኝም። መዝ 37፡20፤10

8. **እግዚአብሔር ያለፈውን አሳዛኝ መታሰቢያችንን እንዴት አድርጎ ይደመስሰዋል?**

“እግዚአብሔርም እንባን ሁሉ ከአይናቸው ያብሳል፤ ሞትም ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም፤ ኃዘንም ቢሆን ወይም ጩኸት ወይም ስቃይ ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም የቀደመው ስርዓት አልፏልና” ራዕይ 21፡4

እንዴት ያለ ቸር አምላክ ነው? ለሚጠፉት ልቡ ይራራል። በተወደደው ርህራሔው ኢየሱስ ትልቁን የምህረት መሐረቡን ወስዶ እንባቸውን ያብሳል። ያለፈውንም አሳዛኝ መታሰቢያዎ ያብሳል። በኢሳያስ 65፡17 እንዲህ ይላል። “እነሆ፥ አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር እፈጥራለሁና፤ የቀደሙትም አይታሰቡም፥ ወደ ልብም አይገቡም።” የጠፉት ስቃይ ሲቀበሉ ፍጹም ከሆነው መጨረሻ ይደርሳሉ።

9. **ልዩ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች**

መጽሐፍ ቅዱስ ግን ስለዘላለም ስቃይ “ከዘላለም እስከዘላለም” ስለሚቆየው “የዘላለም እሳት” “ስለማይጠፋው እሳት” አይናገርምን? ብለህ ትጠይቅ ይሆናል። (ይህ ክፍል በጣም አስቸጋሪ ቢመስልህ ቅር አይበልህ። ጥናትህን ቀጥል። በሙሉ ለመረዳት ስፍራው የማይፈቅድ በመሆኑ ባጭሩና በጥቂቱ ብቻ መግለጫዎች ተሰጥተዋል።

ከዘላለም እስከዘላለም - ራዕይ 14፡11 “ከዘላለም እስከዘላለም” እያሉ የሚናገሩ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉ ይህን የሚመስሉ ጥቅሶች የሰውን የዕድሜውን ጊዜ ለመናገር ብዙ ጊዜ ይጠቀሳሉ። የጊዜውን አኳኋን እስኪለውጠው ድረስ ስላልተወሰነ ጊዜ የሚናገሩ ቃላት ናቸው። 2ነገ 5፡27 ፣ ዘፀ

21፡6 ፣ 1ሳሙ 1፡22። በዮናስ 2፡7 ነቢዩ ሶስቱን ቀናት ብቻ "ዘላለም" ብሎ ይጠራቸዋል። እንግዲህ "ዘላለም" የሚለው ቃል ፈጽሞ ኃጢአተኞቹ ዘወትር እንደሚቃጠሉ የሚያስረዳ ቃል አይደለም።

**የዘላለም እሳት** - ይሁዳ ስለሁለት ዓመጸኞች ከተሞች ስለሰዶምና ገሞራ በአብርሃም ዘመን በ"ዘላለም እሳት" ጠፍተው እንደነበር ይናገራል። እነሱ ግን አሁን እየተቃጠለ አይደለም። በሰዶምና በገሞራ ያነበሩትን ኃጢአትና ኃጢአተኞችን ያጠፋው የማይጠፋው የእግዚአብሔር እሳት ካጠፋና ከጨረሰ በኋላ መቃጠሉን አቁሟል።

**የማይጠፋ እሳት** - ማርቆስ 9፡43-48ን አንብብ። ከየሩሳሌም በስተውጪ ቆሻሻና የሞቱ እሰሶች የወንጀለኞችም ቡድኖች የሚጣልበት የገሃነም ሸለቆ ነበር። በዚያ ሸለቆ ያለው እሳት ሁልጊዜ ይቃጠል ነበር። ከዚያ የነበሩትም ትሎች ከእሳቱ የቀረውን ይበሉ ነበር፡፤ አንዳንዶች የመጽሐፍ ቅዱስ ተርጓሚዎች ይህንን ገሃነም የተባለውን ቃል ሲኦል ብለው ተርጉመውታል። በዚያን ጊዜ በሚኖሩት አይሁዶች ዘንድ ‹‹የማይጠፋ እሳት›› (ማቴ 3፡12 ተብሎ የሚጠራ ስለነበረ) ነው። ደግሞም የሩሳሌምን አጥፍቷል (ኤር 27፡17) ያ እሳት ግን የሩሳሌምን ፈጽሞ እስኪያጠፋ ድረስ ብቻ ሲነድ ቆይቷል። በዓለም ፍጻሜም እንደዚሁ ይሆናል። ከስድስተኛው እስከ ዘጠኛው አንቀጽ ያየናቸው ጥቅሶች ኃጢአተኞች ምድርን በሚያነጻው እሳት ፈጽመው እንደሚጠፉ በግልጽ ያሳያሉ፡ ፡ የኃጢአት ምልክቶችና ኃጢአተኞች ሁሉ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ተለይተው ለዘላለም ይወገዳሉ።

10. **ኢየሱስ ስለሚጠፉት ሰዎች ምን ይሰማዋል?**

"እኔ ሕያው ነኝና ኃጢአተኛው ከመንገዱ ተመልሶ በሕይወት ይኖር ዘንድ እንጂ ኃጢአተኛው ይሞት ዘንድ አልፈቅድም፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር፤ የእስራኤል ቤት ሆይ፥ ተመለሱ፥ ከክፉ መንገዳችሁ ተመለሱ ስለ ምንስ ትሞታላችሁ?" ሕዝቅ 33፡11

እንዲህ ከሆነ ሕዝቦች አሁን የሱስን ለምን አይሰሙትም? ፍቅሩን አሁኑኑ ተቀብለው በሁሉ መንገድ የማይከተሉት ለምንድን ነው? ጊዜው በጣም እስኪያልፍባቸው ድረስ የሱስን ሳይታዘዙ ለምን ይቆያሉ? በኃጢአታቸውስ ለምን ይሞታሉ?

11. **ኢየሱስ ኃጢአተኞ ሲሞቱ ምን ይሰማዋል?**

"እግዚአብሔርም ሥራውን ማለት እንግዳ ሥራውን ይሠራ ዘንድ፥ አድራጎቱንም ማለት ያልታወቀውን አድራጎቱን ያደርግ ዘንድ" ኢሣ 28፡21

ኃጢአተኞችን ለማጥፋት የሚደረገው የሚያስፈራ ሥራ ለኢየሱስ ‹‹እንግዳ ሥራ›› ነው። በሕይወቱ ሙሉ ሰዎችን ለመርዳትና ለማዳን ሲሞክር ቆይቶ ተሠዋ። ኢየሱስ ሕይወቱን የሰጠላቸው ሲሆን ልመናውን የናቁትን ለማጥፋት በመጨረሻ ‹‹እንግዳ ስራውን›› ‹‹ያልታወቀውን አደራረጉን›› ለመፈጸም በመጣ ጊዜ ለርሱ የሚያሳዝንና ልብን የሚሰብር ሰዓት ይሆናል።

ከጥቂት ዓመታት በፊት አንድ እንግዳ የሆነ ታሪክ በጋዜጣዎች ታትሞ ነበር። በአንድ አገር ወንጀለኞችን የሚቀጣ ክፍል በአንድ እሥር ቤት አንድን የከፋ ነፍሰ ገዳይ በኤሌክትሪክ እንዲገድል ይታዘዛል። ያ የሚያስፈራው ሰዓት ደረሰ። ሕግ አስፈጻሚው ክፍል ወንጀለናውን ለመግደልና ትዛዙን ሊፈጽም መጣ። ሕጉን ከሚያሰጽሙት አንዱ ወንጀለኛው የልጅነት ጓደኛው የነበረ መሆኑን ባወቀ ጊዜ እንዴት በጣም ደነገጠ። ረጅም ጊዜ ተለያይተው ይኖሩ የነበረ ሲሆን እስከሚያስፈራው ሰዓት ድረስ አልተገናኙም ነበር። ልበ ደንዳናው ወንጀለኛ የልጅነት ጊዜ ወዳጁን በተገናኘ ጊዜ ልቡ ተነካ። ገዳዩ እያመነታ እንዲህ አለው "ይህን እንዴት ላደርግ እችላለሁ? ሕይወትህንስ ለማጥፋት እንዴት ይቻለኛል? አለ። እስረኛው ግን እያዘነ እንዲህ ሲል መለሰለት። "ወዳጄ ይህን ማድረግ አለብህ። ኡህ ሞት ይገባኛል። በኃጢአት ኖሬያሁ፤ ሕግንም ጥሼያለሁ ነፍስንም ገድያለሁ መሞትም ይገባኛል፤ አንተ ተግባርህን ብቻ መፈጸምህ ነው። እኔም ቂም አልይዝብህም"። ልክ እንደዚህ ታሪክ ሁሉ ጌታችንም በበደለኛው ሞት ደስ አይሰኝም።

12. **እንዴት ያለ አስፈሪ ጊዜ ይመጣ ይሆን?**

"እኔ ህያው ነኝ ይላል ጌታ ጉልበት ሁሉ ለእኔ ይንበረከካል። ምላስም ሁሉ እግዚአብሔርን ያመሰግናል ተብሎ ተጽፎአልና። እንግዲያስ እያንዳችን ስለ ስራችን ለእግዚአብሔር መልስ እንሰጣለን" ሮሜ 14፡11-12

ኃጢአተኞች በፈራጁ ፊት ቆመው ችላ ያሉትንና ያላወቁትን ወይም የናቁትን የኢየሱስን ፊት ሲያዩ የሚያስፈራ ቀንይሆናል። ኢየሱስ ሊያድናቸው የተቻለውን ሁሉ አድርጓል። በሀፍረት አንገታቸውን እንደደፉ ያለ ምክንያት ሁላቸው እየጮሁ "ኢሱስ ክርቶስ ጌታ ነው፤ ቅንም አምላክ ነው።" ይላሉ።

በሚገባ ቆም ብለህ አስብ ማንም ሰው እንዲድን የተሰጠውን ምቹ ጊዜ ካልናቀና ቸል ካላለ በስተቀር አንድም ሰው አይጠፋም። ኢየሱስን አዳኛቸው አድርገው የሚቀበሉትን ሁሉ ያድናቸዋል። ነገር ግን በኃጢአቱ የቀጠለውን ማንንም ቢሆን አያድነውም። እነዚያ እያወቁ በኃጢአት የጸኑ ሁሉ የሞት ቅጣት (ሁለተኛው ሞት) ይጠብቃቸዋል።

13. **ዓለም በመጨረሻ ከኃጢያት ፍጹም የሚነጻ ከሆነ አሁን እንዴት ያለ ኑሮ ልንኖር ይገባል?**

"ይህ ሁሉ እንዲህ የሚቀልጥ ከሆነ፥ የእግዚአብሔርን ቀን መምጣት እየጠበቃችሁና እያስቸኰላችሁ፥ በቅዱስ ኑሮ እግዚአብሔርንም በመምሰል እንደ ምን ልትሆኑ ይገባችኋል? ስለዚያ ቀን ሰማያት ተቃጥለው ይቀልጣሉ የሰማይም ፍጥረት በትልቅ ትኵሳት ይፈታል፤ነገር ግን ጽድቅ የሚኖርባትን አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር እንደ ተስፋ ቃሉ እንጠብቃለን።ስለዚህ፥ ወዳጆች ሆይ፥ ይህን እየጠበቃችሁ ያለ ነውርና ያለ ነቀፋ ሆናችሁ በሰላም በእርሱ እንድትገኙ ትጉ፥"2ጴ 3፡ 11-14

እግዚአብሔር በኃጢአት የተጨማለቀውን ይህንን ዓለም በቅርብ ጊዜ ኃጢአትን ፍጹም ሊያነጻ በሚችለው እሳት ያቃጥለዋል። ይህንንም የሚያደርግበት ምክንያት ዓለምን ከኃጢያት መታሰቢያ ከመሆን ነጻ ለማድረግ ነው። በመሆኑም ኃጢአት ካለበት ቦታ ሁሉ ይጠፋል። ስለዚህ በመጨረሻቀን እንዳትጠፋ ኃጢአትን እንድትተው ዛሬ በምህረቱ ይለምንሃል።

14. **ወደ ሰማይ እንዳይገቡ የሚከለከሉ እነማን ናቸው?**

"ለበጉም በሆነው በሕይወት መጽሐፍ ከተጻፉት በቀር፥ ጸያፍ ነገር ሁሉ ርኵሰትና ውሸትም የሚያደርግ ወደ እርስዋ ከቶ አይገባም።" ራዕ 21፡27 "በሕይወትም መጽሐፍ ተጽፎ ያልተገኘው ማንኛውም በእሳት ባሕር ውስጥ ተጣለ።"ራዕ 20፡15

ኃጢአትን ትተህ አሁኑኑ ልብህን ለኢየሱስ ስጥ። ምክንያቱም በኃጢአት የረከሰ ልብ ወደ ሰማይ አይገባምና። የሱስን በመስቀል ላይ የቸነከረው ኃጠአት ነውና። እንግዲህ በኃጢአት አትጸና የሱስም ከኃጢአትህ እንዲያነጻህና ስምህ በሕይወት መጽሐፍ እንዲጻፍ ራስህን ለእርሱ አስረክብ።

15. **ኢየሱስ ይቅርታ ለመስጠት ምንኛ ይናፍቃል?**

"መተላለፍህን፦ ስለ እኔ ስል የምደመስስ እኔ ነኝ ኃጢአትህንም አላስብም።" ኢሳ 43፡25

ኢየሱስ ይቅር ብሎ ሊያድንህ ይፈልጋል። የአንድ ኃጠአተኛ መጥፋት እርሱን እጅግ ያሳስበዋል፤ ስለዚህ አየሱስ ሆይ ሁሉን ላንተ አስረክባለሁ በማለት ራስህን ለእርሱ ዛሬውኑ አስረክብ።